# ይድረስ ለያፌት ዓምደ

## “ትግራዋይ ከፅንኞች እንዴት ይታረቅ?” ደራሲ (በዓይጋ ድህረ ገፅ የቀረበ)

## ከጋይም ህዝቢ

ክቡር ያፌት ዓምደ

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታዉቃል እንደሚባልዉ የርስዎም ፅሁፍ ገና ከርእሱ ምንነቱ ይናገራል። ትግራዋይ ከፅንፈኞች እንዴት ይታረቃል? ያሉቱ ለትግራይ ህዝብ እንግዳ የሆነ የፈጠራ ወሬ ነው። ተጋሩ “ፅንፈኛ“ ከሚባል አካል ጠላትነት የለዉም። አለያም ፅንፈኞች የሚልዋቸዉ የተጋሩ ጠላቶች በስርአት ግለፅ ያድርጉዋቸዉና እኔም ሆነ ሌሎች ተጋሩ ከጠላቶቻችን እንድንጠነቀቅ ያገላግለናል። ልነግርዎት የምፈልገዉ ግን ተጋሩ ጠላት የለንም። በሃይማኖታችን ይሁን በቅዋንቅዋችን፡- በጎሳችን ይሁን በባህላችን፡- በታሪካችን ይሁን በኢትዮጵያዊ ዜግነታችን ትግራዎት ጠላት የለንም። ምነዉ ያዋቂ ደንቆሮ መሆን አማርዎት።

ክቡር ያፌት ዓምደ የታሪክ አዋቂ መሆንዎን ለመግለፅ የከጀሉ ይመስላል። እዉነትም የታሪክ አዋቂ ነዎት። ሆኖም ግን በየተኛዉ የጊዜ ታሪክ ነው ያሁንዋ የትግራይ ክፍለ ሀገር የትናትናዋ የአክሱም ግዛት የነበረችው ? የአክሱም መንግስት ብያንስ እስከ ቀይ ባህር ድረስ እንደነበረ ይተረክለታል። ምነዉ የርስዎን ታሪክ በትግራይ ክፍለ ሀገር ብቻ መኖርዋን ያስተምራል ? ያኔም የቅዋንቅዋ ክልል ኖሮ ይሆን ? ምን አዉቃለሁ የታሪክ ምሁር አይደለሁም እና! የሀገሩ ታሪክ ያማያዉቅ መሃይም እንደማይሉኝ ከወዲሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

ክቡር ያፌት የሚመኩብን የሚኩራራብን ከኛ (ከተጋሩ) በላይ ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ “የህብረተሰብ ክፍሎች“ ብለዉ የጠቀስዋቸዉ እንዲነግሩኝ እማጠንዎታለሁ። ዋስ ጥሩ ሙግት ግጠሙኝ እንድላቸዉ። ይህ ካልሆነ ግን እኔ የክልልዎ ልጅ አልጠቀሙኝም። አስጠቁኝ እንጂ። ሚስጥር አድርገዉ ልግልዎ አይያዙት። ወገንን ማስተማር ጥሩ ስነምግባር ነው። ለወገንዎ አያ ካልሆኑ አስተማሪ ካልሆኑ ምኑን ፈየዱ ታድያ። አለያም ችግሩን ብቻዎን ሊወጡት ፈልገዉ ነው ? ተጋሩትን ላለማስቸገር ? በጣም ለወገን የሚቆረቆሩ ትግራዋይ ነዎት። ተስፋ ግን አደርጋለሁ እኛ ብቻ ነን ኢትዮጵያዉያን የሚሉቱ “የህብረተሰቡ ክፍሎች ፡ የፈጠራ ውሸት እንዳይሆን። እንድታዘብዎት አልፈልግምና። ግን እኮ ያገሬ ሰው ኢትዮጵያዉያን አይደላችሁም የሚሉንን አብረን ብንፋለማቸዉ አይሻልም። ማለት “ ዝሓበራ ኣፃብዕቲስ ጣምራ ኣርቃይ ይሰብራ “ እንደምንለዉ አባባል። ይህ ሁሉ የምልዎት እንደዚያ የሚሉ በህይወት ገጥሞኝ ስለማያዉቅ ነው። ተሓህት/ተወህት ግን ከኢትዮጵያ ነፃ መዉጣት አለብን እያሉ ሲያስተምሩን ጊዜዉ ራቅ ይበል እንጂ አስታዉሳለሁ። አሁንም እነሱ ይሆን ኢትዮጵያዉያን አይደላችሁም የሚሉን!?? አይፍረዱብኝ እንደርስዎ እውቀቱ ስለሌለኝ ነው። ሓደራ ግና ትግራዋይ ኣይኮንካን ክይብሉኒ። ለጉዴ ባእድ ስለሆንኩኝ። የተማረ ይግደልኝ የሚባለዉ ለካ እርስዎን መሳይ ምሁር ነው። አጀብ።

አቶ ያፌት በስልጣን ላይ ያሉት የትግራይ ልጆች ስለሆኑ ኢ.ህአደግ ይልዋቸዋል ያሉቱ ያባባል ግድፈት ነው ብየ ወስጀዋለሁ። ሆኖም ግን የትግራይ ልጆች ስለሆኑ ኢ.ህአደግ ይሉዋቸዋል ሲሉ ለማደናገር የተጠቀሙበት ደግሞ መሰለኝ። ህወሓት/ወያነ ይሉዋቸዋል ለማለት ይሆን? ግድ የለም ኢ.ህአደግ የወያነ የጡት ስም ነው ብየ አልነግርዎትም። መድሓርሓሪ ወይም በዛሬዉ አባባል ነፍጠኛ መባል አልፈልግምና። ----- የወያነ ደጋፊ ከሆነ ------ በምናደርገዉ ትግል አይቀላቀልም ይላሉ ብለዉ አስፍረዋል፡- ለመሆኑ የኢትዮጵያዉያን ትግል ወያነን ከስልጣን ለማስወገድ እና ህዝባዊ መንግሰት ለማንገስ የሚደረግ ትግል መሆኑን ያዉቃሉ? ምነው የዋህ ለመሆን አማርዎት። አብረዉ መታገል የሚችሉት ተመሳሳይ የሆነ የፖለቲካ ይዘት ያላቸዉ፡- የጋራ ጠላት ያላቸዉ፡- ለህዝብና ለአገር ሉኡላዊነት፡- ለዲሞክራሲ ስራአት ተገዥ የሆኑ ናቸዉ። ህወሓት ይህንን አታሟላም ስለሆነም ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ይሁኑ ኢትዮጵያዉያን አይፈልግዋትም። መርዶ አይሁንብዎት። ከዚህ በመለስ ግን ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ይሁን ገለሰብ ከኔ ጋር ካልታገላችሁ ብሎ አያስገድድም ወይም አያስርቀም። ይልቁንስ ተሓህት/ወያነ “ትግል“ ስትጀምር ታደርገዉ የነበረዉን አስታወሱኝ። የትግራይ የአርሶ አደር ልጆች (በእድሜ ህፃናት የሆኑ) የጠመንጃዋ አንጋቾች እንዲሆኑ ህዝቡም የግድ ጠባብ ፖለቲካዋን እንዲከተል ታደርገዉ የነበረዉን አስታወሱኝ። እርስዎም ትግራዋይ ስለሆኑ የቅርብ ምስክር ነዎትና ይህንን ሃቅ አሌ እንደማይሉት እተማመናለሁ። እምቢ ያሉትም ምን አይነት እርምጃ ትወስድባቸዋ እንደነበረች ለርሰዎ ዘርዝሮ መናግር ልጅ ለናት ምጥ አስተማረች ስለሚሆንብኝና እርስዎንም መዳፈር ስለሚሆንብኝ ከዚሁ አላካትተዉም። ማለት መግደሉን ማሰቃየቱን ከመሬት በታች ባዶ

ሹዱሽተ ማሰሩ ሴት ልብስ አልብሶ አንቀልባ ማሳዘሉ ኢሕአፓ መድሓርሓሪ "ጃሱስ" መወንጀሉን የመሳሰሉት  ማለቴ ነው።

ያፌት ዓምደ  ያላማ ልዩነት በሚል ርእስ ያቀረቡት ሃሳብ ምን ለማለት እንደፈለጉ ለመረዳት አልቻልኩም እና ይቅርታዎን ከወዲሁ ልጠይቅዎት። እሰጣ ገባ ሆነብኝ። ደፈረኝ አይበሉኝ እንጂ ለመሆኑ ለአንባብያን ከማቅብዎ በፊት መልሰዉ አንብበዉት ነበር? ግድፈቶች ካሉበት እርማት ለማድረግ ብዬ ነው። ግን እኮ ፍፁም ነዎትና አስፈላጊም አይደለም። ይቅርታ። ሆኖም ካሰፈሩት አንዳንድ ለማለት ልሞክር። ወያነ ለትግራይ ህዝብ ጠላት አይደልም ብለዉ ምስክርነትዎን አቅርበዋል። ለመሆኑ ጠላት ሲባል ምን አይነት ነው። እንደሚመስለኝ ጠላት ማለት፡- የሚገድል የሚያስር ሰብአዊ መብት የሚነፍግ ለህግ የማይገዛ ወዘተ የሚያካትት ማለት ነው። ታድያ የትግራይ ህዝብ ይህ ሁሉ ግፍ ላለፉት 38 አምታት አልደረሰበትም? አዎ በተሓህት/ህወሓት ተብላ በምትጠራዉ ድርጅት። ለርስዎ ማስረጃ ማቅረብ የለብኝም። ለቀባሪ አስረዱት ይሆንብኛልና። ብሎም ለተጋሩ ጥብቅና ይቆማሉ ብዬም ስለምተማመንዎት። እናም ይህ ሁሉ ሰቀቀን የተፈረደበት ህዝብ ለምን ጠላት አይሆንም። አዎ ወያነ የትግራይ ህዝብ ጠላት ናት። እንቆቅልሽ አይሁንብዎ። በማከልም " ከሌሎች "ኢትዮጵያዉያን " በተለይ " ካክራሪዉ/ፅንፈኞች ድያስፖራ" ጋር ያለዉ ልዩነት" ብለዉ ያሰፈሩት የተንጠላጠለ ሀረግ ሆነብኝ። ተጋሩትን ነው " ከሌሎች "ኢትዮጵያዉያን" ---- ያለዉ ልዩነት የሚሊቱ? ከሆነ ምነው የሩቅ ምስክር መሆን አማርዎት? ተጋሩ በምኑ ነው ከሌሎች ኢትዮጵታዉያን ልዩነት ያለን ? ተጋሩ ኢትዮጵያዉያን አይደለንም ማለትዎ ይሆን? ለዚህም ይሆን ኢትዮጵያ የሚለዉን በትምህርተ ጥቅስ ያስቀመጡት? ለመሆኑ "ፅንፈኛዉ ዳያስፖራ" ማን ነው? ምንድን ነው? ከባእድ ፅንፈኛ ተጋሩ ምን አገባን? ምነው ሁሉን ማደነቋቆል ተማኙ።

ክቡር ያፌት  አዎ ተጋሩ በኢትዮጵያ ህዝባዊ ስርአት ለማንገስ ታግለዋል። ይህን አሌ የሚል የለም። ታድያ ትግላቸዉ በፋሽሽቶች ጠባቦችና ተኝጣዮች ተቀማ እንጂ። አሁንም ጠባቦችን አስወግዶ የኢዮጵያ ህዝብ በበላይነት የሚገዛዉ ዲሞክራስያዊ ስርአት ለማንገስ ትግሉን ይቀጥላል። እየቀጠለም ነዉ። አሁን በስልጣን ላይ ያሉቱ ካብራኩ የተፈጠሩት እንደ ባእድ ጠላት የሚገዙት ገና ከጥዋቱ ስለሚያዉቃቸዉ ጊዜ የፈጠራቸዉ ፀረ ኢትዮጵያ ናቸዉና በኢትዮጵያዊነቱ ብሎም በትግራዋይነቱ ይፋለማቸዋል። አያ ያፌት ተጋሩ ኢትዮጵያዉያን ነን። መርዶ አይሁንብዎት።

አቶ ያፌት በነገብሩ አስራትና ስዬ ኣብርሃ የተቹት ቂ ቂ ቂ አሰኘኝ። የፈለጉት ይበልዋቸዉ ዳንታም የለኝ። ጅራፍ ራስዋ መታ ራስዋ ትጮሀለች ይባል የለ አይገርመኝም። ለኔ መለስ  ስዬ  ገብሩ ሌሎች የወያነ መሪዎች ምንም ልዩነት የላቸዉም። አንድም ሁለትም ናቸውና። አንድ ናቸዉ ስልዎት ያለምክንያት አይደለም። ካልዘነጉት ወይም ያልሰሙ ካልሆነ በስተቀር መለስ ባንድ ወቅት ኢትዮጵያ የመቶ አመት እድሜ ያላት ሰንደቅ አለማችንም ጨርቅ ነው ብሎ ለትዮጵያ ህዝብ ተናግሮ ነበር። ታድያ የ፪ሺ አመታት ሲያከብር የሰንደቅ አለማ ቀን ብሎ ደግሞ ሰይሚል።ታአምር ነው አይግምዎት። ባንድ ራስ ሁለት መላስ የወያነ መሪዎች መለያቸዉ ነው። ስለሆነም ስዬም ሆነ ገብሩ ቃላቸዉ ቢያጥፉ አዲስ ነገር አይደለም። አቶ ያፌት ምነው ለወያን ባእድ መሆን መረጡ። ዛሬም እንደትናንትናዉ በተጋሩ ስም ለመንገድ ዓረና ትግራይ ብለዉ ሁለተኛ ስም ይዘዉ ብቅ ቢሉ ሳታማሃኝ ብላኝ ማለቱ ይበጃል። ለመሆኑ ዓረና ትግራይ ሲሉ ለምን ይሆን? ዓረና በአማርኛ ሲተረጎም ተስተካክለናል ታርመናል (ከስህተት ወይም ከጥፋት) ማለት ነው። ተጋሩ ምን ተሳሳትን ምን አጠፋን ? ይቅርታ የምንለዉ ላማን ነው ? አይድነቅዎት ዛሬም እንደትናንትናዉ ቅጥፈታቸዉ እንደቀጠለ ነው። ለማንኛዉም አያ ያፌት ያዉቅዋቸዋልና በቃችሁ በህዝብ ህይወትና ደም መንገዱ ያክትም ምእራፍ አድርጉበት ብለዉ ይንገርዋቸዉ።

ክቡር ያፌት ዓምደ  ለማጠቃለል ሊፅፉት የፈለጉት ሃሳብ የረሱ መሰለኝ። ትግራዋይ ከፅንፈኞች እንዴት የታረቅ ብለዉ ርእስ ከሰጠ በኋላ አንዳችም ነገር ሳያሰፍሩ በትናንት የወያነ መሪዎች ፅህፉዎን ደመደሙት። ዘንግተዉ ነው ወይስ ብቃቱ የለም? ዉሸት ለመፃፍ ቀርቶ ለመናገርም ያስቸግራል። መንተባተብ ብቻ ነው የሚሆነዉ። እናም ታዘብኩዎት። ሌላ ጊዜ ሃሳብዎን ለመፃፍና ላንባቢያን ለማቅረብ ሲፈልጉ መጀመርያ ሃሳብዎን ይንደፉ ከዛም በቅድመ ተከተል ዝርዝሩን ይፃፉ። ክቡር አቶ አቤ ጉበኛ " የምሁራን ደንቆሮዎች" ከሚላቸዉ ከመዘነቅ ያድንዎታልና።

## ኢትዮጵያ ለዘልአለም ትኖራለች ! ! !

**05-30-2009**